# እዘኝልኝ ድንግል

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ (፪)
እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ (፪)

ያንን የእሳት ባህር እንዳላይ አደራ
ድረሽልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ (፪)

አዝ...

የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድኃኒት ንኢ በደመና (፪)

አዝ...

አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ (፪)

አዝ...

አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማጸንሻለሁ በደሌን አውቄ (፪)

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org